# የታዳጊ ልጆችዎን ከአደጋ መከላከልና ጥንቃቄ

በቅድመ ህፃንነት የጤና እና ደህንነት ጉዳይ ላይ ከብሄራዊ ማዕከል ለወላጆች የተሰጠ ጠቃሚ መረጃ

## ለታዳጊ ልጆችዎ የሚደረግ የአደጋ መከላከልና ጥንቃቄ

- ለልጆችዎ እድገትና ትምህርት ከአደጋ የተጠበቀ ቦታ መኖሩን ያረጋግጡ
- ልጆችዎን ከአደጋ ይጠብቁ
- ልጆችዎ ከአደጋ እንዴት መጠበቅ እንዳለባቸው ያስተምሯቸው



### ይህ ምን ጠቀሜታ አለው?

### ልጆች ለመመራመር ይፈልጋሉ፤ ነገር ግን

- ለጨዋታ ደህንነቱ የተጠበቀ ቦታ
- አዋቂዎችን እያዩ እና ከእነሱ እየተማሩ አደጋ ከመከሰቱ በፊት እንዴት መማር እንዳለባቸው ይማራሉ
- ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ አዳዲስ ክህሎቶችን የሚለማመዱበት አጋጣሚዎች

### ልጆች ደህንነታቸው የተጠበቀ ሲሆን ወደ ፊት ሊሆኑ የሚችሉት፤

- ከአደጋ የተጠበቁ ይሆናሉ
- ትምህርታቸው ላይ ያተኩራሉ
- አዳዲስ እውቀቶችን በራስ መተማመን ይፈልጋሉ

## ልጆችዎን ለማገዝ ማድረግ የሚገባዎት ተግባራት

- በቤት ውስጥ
  - Kመድሃኒት፣ የጽዳት እንዲሁም አደገኛ ምርቶችን ልጆችዎ ከሚያገኙበት ቦታ ማራቅ
  - የሳጥን ቁልፎችን መጠቀምና የኤሌክሰትሪክ ሶኬቶችን መሸፈን
  - በደረጃ መውጫ ላይ የደህንነት ጥንቃቄ በሮችን መጠቀም
  - የደረጃ መወጣጫዎችን የመደገፊያ እጅታ ያላቸወ እንዲሆኑ ማድረግ
  - የመስኮት ጠርዞችን ልጆች ከሚደርሱበት ርቀት በላይ ማድረግ
  - ረጃጅም ገመድ ያላቸው ኤሌክትሪክ ገመዶችን በተቻለ መጠን አለመጠቀም፤ ይህ የማይቻል ከሆነ ግን ህጻናት ከማይደርሱበት ቦታ ማድረግ።
  - ልጆችን በጀርባቸው እንዲተኙ አድርጎ ለስላሳ የሆነ ብርድ ልብስ ትራስና መታቀፊያዎችን አይደርቡላቸው።
  - ልጆችን ትኩስ ከሆኑ ምግቦችና ፈሳሾች እንዲርቁ ያድርጓቸው።
  - የብረድስት እጀታዎችን ከማብሰያው ስቶቭ ጀርባ እንዲሆን ያድርጉ።፡
  - የውሃ ማሞቂያውን ቴርሞስታርት 120 ዲግሪ ወይም በታች እንዲሆን ያድርጉ።
  - ልጆችዎ ከእሳት ወይም ከማሞቂያዎች እንዲርቁ ያደርጉ።
  - በሁሉም የቤትዎ ክፍሎች ውስጥ የጭስ ማንቂያ ድምጽ መስጫ መኖሩንና በጸደይ እና በበጋ ወራት ባትሪው መቀየሩን ያረጋግጡ።
  - አስገጥመው ያልሆኑ ከሆነ የካርቦን ሞንኦክሳይድ ጠቋሚ መሳሪያ በቤት ውስጥ ያስገጥሙ።
  - ከአካባቢው የእሳት መከላከያ ጣቢያ ጋር በመሆን የጭስ አላርምንና የካርቦን ሞንኦክሳይድ ጠቋሚ መሳሪያ ከየት ማግኘት እንደሚችሉ እርዳታ ይጠይቁ።
  - ልጆች እንዲታነቁ የሚያደርጉ አነስተኛ መጠን ያላቸው ምግቦችና እቃዎችን በተመለከተ ከህክምና ባለሙያው መረጃን ይጠይቁ።
  - ከአደጋ የማምለጫ እቅዶችን ያዘጋጁ ተግባራዊም ያድርጉ።

# ልጅዎን በዚህ እረገድ ለመርዳት ምን ማድረግ አለብዎት።

- ከቤት ውጪ፥
  - የጸሐይ መከላከያ ይጠቀሙ።
  - ልጆች ከጎዳና ላይ እንዲርቁ ያስተምሯቸው
  - ሳርና አቧራ ካለባቸው መስኮች ይልቅ ልጆችዎ ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ የሚለማመዱባቸው ለስላሳ መስኮችን ይፈልጉ።
  - በመጫወቻ መስኩ ላይ የልጅዎን እንቅስቃሴ በጥንቃቄ ይመልከቱ።
  - መርፌ ቁልፍ ወይም የልብስ ማያያዣ ቁሶችን ከልጅዎ ልብስ ላይ ያስወግዱ።
  - የልጆችዎን የጫማ ማሰሪያ፣ አጭርና የታሰሩ መሆናቸውን ያረጋግጡ።
  - የውሃ የጥንቃቄ ደህንነት
  - ህጻን ልጅ አፍና አፍንጫውን የሚሸፍነውን የውሃ አካል ሁሉ ወደ ሰውነቱ ሊያስገባ እንደሚችል ይገንዘቡ።
  - ልጅዎ በውሃማ አካላት አካባቢ በሚሆንበት ጊዜ በቅርበት ሊያዝ በሚችልበት ሂደት ሁልጊዜ መሆን እንዳለበት ያረጋግጡ።
  - የዋና ትምህርት ይውሰዱ እና ልጅዎንም የባለሙያ ቁጥጥር ባለበት የዋና ትምህርት እንዲወስድ ያድርጉ።
  - በመዋኛ ገንዳ ዙሪያ በአራቱም ማእዘናት አጥር ያለው መዋኛ መኖሩን ያረጋግጡ።
  - በአደጋ ጊዜ የትንፋሽ አሰጣጥ የመጀመሪያ ህክን ዘዴ እርዳታ (ሲፒአርን) ይማሩ




- የተሽከርካሪና የመኪና አደጋ ጥንቃቄ
  - የመኪና ውስጥ የልጆች መቀመጫዎችን ለልጆችዎ እድሜ፣ ቁመትና ክብደት ተመጣጣኝ አድርገው ይምረጡ።
  - ተሽከርካሪዎ ውስጥ የተገጠመው የልጆች መቀመጫ አግባብነት ያለው ይሁን እንዲሁም ሁሉጊዜም ይጠቀሙት።
  - በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን የሂድስታርት ሰራተኛውን ደህንነቱ በተጠበቀ መንገድ የተሽከርካሪ ውስጥ የልጆች መቀመጫ እንዴት እንደሚገጥሙ ይጠይቁት።
  - ከ13 አመት እድሜ በታች የሆናቸው ህጻናት የኋለኛው ወንበር መቀመጫ ላይ ብቻ እንደሚቀመጡ ያረጋገግጡ።
  - አዋቂ ሰው በሌለበት ልጆችዎን በጭራሽ መኪና ውስጥ ትተው አይሂዱ።
  - ለልጆችዎ ተሽከርካሪዎች ለጨዋታ ተስማሚ ያልሆኑ እና አደጋ ሊያስከትሉ እንደሚችሉ ያስተምሯቸው። የተሽከርካሪው መስኮቶች የተከፈቱ ቢሆንም እንኳን ልጆችዎን ተሽከርካሪው ውስጥ ጥሎ መሄድ በመጀመሪያዎቹ 10 ደቂቃዎች ውስጥ ልጆችዎ ላይ ከመጠን በላይ የሆነ ሙቀት የመፈጠር አደጋ ሊያስከትልባቸው ይችላል።

